

# እናመሰግንሃለን

# ያውቃሉን ?

ከዚህ ምድር ምንም ይዘው መሄድ አለመቻልዎን ?
አዎን ! ምንም ! ምንም ሳይወስዱ ይሸኛሉ ::
ሰው ከራራልዎ -- የሚወዱትን ልብስዎን አልብሶ በክብር ይሸኞታል ::
አንዳች ሳይዙ የሰበሰቡትን በትነው ይጓዛሉ ፤ ይሄዳሉ ::

# ነገር ግን

ወደሚሄዱበት ስፍራ ዛሬ የወደዱትን መላክ ይችላሉ ::
አዎን ! ዛሬ በህይወት ሆነው በወዲያኛው ስፍራ ማከማቸት ይችላሉ ::

" ብልም ዝገትም ፤ በማያጠፋው ሌቦችም ቆፍረው በማይሰርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ ፤ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና :: "

ማቴ 6 ÷ 19 ' 21

ምን ይመርጣሉ ?

በዚህ ? ወይስ በዚያ ? --- በአላቂው ? ወይስ በዘላቂው ?

ምርጫው የእርስዎ ነው ! ዛሬም ጥሩ ቀን ነው ለጅማሬ ::

ያውቃሉ ?

## የተከበረ መኖርያ

" የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል ፤ አባቴም ይወደዋል
ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖርያ እናደርጋለን :: "

ዮሃ 14 ÷ 23

እግዚአብሔር በእኛ መኖር ይፈልጋል ::
እሁድ ብቻ የምናስተናግደው እንግዳ ሳይሆን ፤ መኖሪያው ሊያደርገን ነው የሚወደው ::

ለእረፍታችን ማረፊያ ፤ ለጡረታችን መጦርያ ሳይሆን ዘመናችንን ሁሉ ከጣራው ስር ፤ እርሱን ከለላ በማድረግ በእርሱ እንድንኖር ነው አላማው ::

የመልዕክት አድራሻችን ፤ ቋሚ መታወቂያችን ቤቱ እንድንሆን ነው ጉጉቱ ::

እግዚአብሔር የመነጋገሪያ ርዕሳችን ፤ ታዓምርና ድንቅ ሰሪያችን ፤ የሁሉም ፈጣሪ ፤ መሆኑን ብቻ ሳይሆን የመኖርያ ቤታችንም እንደሆነ እናውቅ ዘንድ ነው
" በእርሱ ሕያዋን ነንና ፤ እንንቀሳቀሳለን እንኖርማለን :: " የሐዋ 17 ÷ 28
በማለት ሁሉ በእርሱ ነውና የዚህ ጌታ ማደሪያው እንደሆን እናውቅ ዘንድ ይወዳል ::

" የከበረ መኖርያ በክብር ይመላለሳል :: "

# ጌጠኛ እጀ ጠባብ

" ያዕቆብም ዮሴፍን በስተርጅናው ስለ ወለደው ፤
ከልጆቹ ሁሉ አብልጦ ይወደው ነበር ፤
በኅብረ ቀለማት ያጌጠ እጀ ጠባብም አደረገለት ። "

ዘፍ 37 ፥ 3

የሽምግልናው ልጅ ቢንያም አይደለም እንዴ ? ታዲያ ምነው ? ዮሴፍ መመረጡ ? መወደዱ ?

" ዓለም ሳይፈጠር ፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን ። " ኤፌ 1 ፥ 4 እንደሚል -- ይሆንን ? ።

" በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ ባረከን " ኤፌ 1 ፥ 3

አዎን -- በተለያዩ በረከቶችም ተባርከናል ፤ ዮሴፍ የተለያየ ሕብር ቀለማት ባለው እጀ ጠባብ እንደተባረከ ።

" በውድ ልጁም እንደ ፀጋው ባለጠግነት መጠን ቤዛነትን አገኘን " ኤፌ 1 ፥ 7
እንደሚል --- ቤዛን ለበስን እንደሚል --- ዮሴፍ በብዙ ሕብር ያማረ እጀ ጠባብን ለበሰ ።

ይህን የፀጋ እጀ ጠባብ ለብሰዋል ?
የፀጋው እጀ ጠባብ በፀጋ እንጂ በስራ ስለማይገኝ በፀጋ ባለፀጋ ወደሆነው ጌታ መጠጋት ነው መንገዱ ።



# አቤል ምፅራይም

" ይህ ለግብፅ ሰዎች ታላቅ ልቅሶ ነው ። "

ዘፍ 50 ፥ 11

ያዕቆብ ! በግብፅ ምድር ሞተ ። በግብፅ ምድር አልቀበርም አለ ። ወደ ከነአን ሊወስዱት ሲነሱ የፈረአን ሎላልት ፤ መኳንንትና ሃያላን ከበቡት ፤ በፅኑ ልቅሶ አጀቡት ። ( ዘፍ 50 ፥ 7 )

ምድር በዕንባ ራሰች ፤ የአጣድ አውድማ ዉዑታ ተሞላ ። ( ዘፍ 50 ፥ 11 ) የከነአን ሰዎች ግር አላቸው ፤ ተደነቁ ፤ የሚቹን ታላቅነት አስተዋሉ ። ታላቅ ባለስልጣን ፤ መኮንን መሆን አለበት አሉ ። ታላቅ ልቅሶ ለታላቅ ነውና ።

ያዕቆብ በታላቅ ልቅሶ ፤ በታላላቆች የታጀበው ስለምን ነው ? ያዕቆብ በግብፅ ተራ ሰው አይደለምን ? ስልጣን የሌለው ፤ ስደተኛ ---- ።

የያዕቆብ ሞቱ የከበረው ከምን የተነሳ ነው ?
በመኳንንት የታጀበው -- ስለምን ነው ?
ግብፅ ያለቀሰለት -------- ለምንድነው ?
" ይህ ለግብፅ ታላቅ ልቅሶ ነው ! " የተባለው ስለምን ነው ?

ያዕቆብ ከልጁ ጋር ካለው ሕብረት የተነሳ ነው የከበረው ። ለያዕቆብ የተደረገው ሁሉ የተደረገው ከልጁ ( ከዮሴፍ ) የተነሳ ነው ። ያዕቆብ በልጁ ከበረ ፤ በመኳንንት ታጀበ ።

እርስዎም :-

ከልጁ ጋር ህብረት ካደረጉ ---- ከልጁ የተነሳ ይከብራሉ ። ልጁም እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ።

ዛሬ ! ከልጁ ጋር የሚደረገው ህብረት ለዛሬም ፤ ለዘለቄታም ክብር ፤ የዘላለም ሕይወትም ነውና ።

" እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደሰጠን
ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው ።
ልጁ ያለው ሕይወት አለው ፤ የእግዚአብሔር ልጅ
የሌለው ሕይወት የለውም ። "

ዮሃ 5 ፥ 11 - 12

# <u>የውዴታ አ ምልኮ</u>

“ ዳዊትም ፡-በበሩ አጠገብ ካለችው ከቤተ ልሔም ምንጭ ውኃ ማን ባጠጣኝ ? ብሎ ተመኘ ። ሦስቱም ኃያላን የፍልስጥኤማውያንን ሠራዊት ቀድደው ሄዱ ፥ በበሩም አጠገብ ካለችው ከቤተ ልሔም ምንጭ ውኃ ቀዱ ፥ ይዘውም ለዳዊት አመጡለት ፤ እርሱ ግን ሊጠጣ አልወደደም ፥ ነገር ግን ለእግዚአብሔር አፍስሶ ፡- አቤቱ ፥ ይህን አደርግ ዘንድ ከእኔ ይራቅ አለ ። “

2ኛ ሳሙ 23 ፥ 15

ይህን ብቻ ነው የምፈልገው ፤ ጉጉቴ ይሄው ነው !
አንድ ብቻ ነው ! ውሃ ---- የቤተ ልሔም ውሃ ።

ዳዊት ከቤተ ልሔም ምንጭ ውሃ ማን ባጠጣኝ ብሎ ተመኘ ።

ሶስቱ ሃያላን የፍልስጥኤማውያንን ሠራዊት ቀድደው ሄዱ ፥ በበሩም አጠገብ ካለችው ከቤተ ልሔም ምንጭ ውሃ ቀዱ ፥ ይዘውም ለዳዊት አመጡለት ።
ምኞት ሲሳካ ፤ እቅድ ሲሞላ እሰየው ነው ።

ዳዊት ፡- በልቡ የወደደውንና በአንደበቱም የገለፀውን አገኘ ፤ ሆነለት ። በሕይወቱ አንደኛ ነው ያለውን ነገር ጨበጠው ፤ የሱ አደረገው ።

ነገር ግን ዳዊት ፡- ይህንን የወደድኩትን ነገር ፤
ምነው ? ባገኘሁት የምለውን ነገር “ <u>ለአምላኬ</u> ” እሰዋለሁ ብሎ ለጌታ አፈሰሰው ።

ያለውን ፤ ያንን የሚወደውን መስዋዕት አድርጎ ለጌታ ሰጠው ----
አምልኮ ------- እውነተኛ አምልኮ ------- ያስከፍላልኮ ?

# <u>የተዘነጋ በረከት</u>

እርሱ ራሱ ፡- “ ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው ” ያለውን የጌታን የኢየሱስን ቃል ልታስቡ ይገባችሁ ዘንድ በሁሉ አሳየኋችሁ ።

የሐዋ 20 ፥ 35

አዎን ! ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ( የተባረከ ) ነው ። መስጠት የእግዚአብሔርን ባሕሪይ ያሳያልና ፤ ከሚቀበለው ይልቅ የሚሰጠው የተባረከ ነውና ።

መቀበልም የሰውነትን ባሕሪይ ያሳያልና እርሱም የተባረከ ነው ። ነገር ግን መስጠት ከመቀበል ይልቅ ብዙ በረከትን ያስገኛል ነው የሚለን ጌታ ።

ጌታ ራሱ የተናገረው ቃል ሆኖ ሳለ ፤ ማቴዎስ ለምን በመፅሃፉ አላሰፈረልንም ፤ ማርቆስና ሉቃስ ዮሃንስስ ስለምን ዘንግተውት አለፉ ?

መንፈስ ቅዱስ በጳውሎስ በኩል ለኛ መግለፁ በመስጠት ያለውን በረከት እንድንቀበል ነውና ልብ ልንለው ይገባል ።

ለእግዚአብሔር መንግስት መስፋት ምን እየሰጡ ነው ?
ገንዘብ ? ጊዜ ? --- ምን ? ------ ራስዎን ? --- ምን ?

ተረስቶ የነበረው የጌታ ቃል ዛሬ ለእርስዎ ሲገለፅ ምላሽዎ ምንድነው ?

ልብ ይበሉ የዘራነውን ያንኑ እናጭዳለንና !

አዎን ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው ።

# ከእርሱ ጋር ----- በእርሱ ከተማ

" ብዙ ሕዝብም ከእርሱ ጋር አብረው ሄዱ "

ሉቃ 7 ÷ 11

ሁለት በርካታ ሕዝብ ናይን በምትባል ስፍራ እናያለን ። አንደኛው ከኢየሱስ ጋር ሆ ! እያለ ወደ ናይን ከተማ ሲገባ ሁለተኛው እያለቀሰ እሬሳ ተሸክሞ ከናይን ከተማ ይወጣል ።

አንደኛው ከኢየሱስ ጋር ስለሚጓዝ ሃሴትን ሲያደርግ ከከተማው በዕንባ የሚወጣው ፣ ተስፋው የሞተበት ፣ ኢየሱስን የማያውቅ ሕዝብ ነው ።

እርስዎ ከየትኛው ወገን ነዎት ?
ከኢየሱስ ጋር ወደ ከተማ ጉዞ ወይስ ያለ ኢየሱስ ወደ ቀብር ?
ከኢየሱስ ጋር ወደ ከተማ ይጓዙ ከሆነ ----- ወደ የትኛው ከተማ ?

ዕብ 11 ÷ 10 " መሠረት ያላት ÷ እግዚአብሔር የሠራትና የፈጠራት ከተማ " ወደ ተባለላት ከተማ ነውን ?

ልብ ይበሉ ፦ አብርሃም የራሱን ከተማ ለቅቆ ወደ እግዚአብሔር ከተማ የተጓዘው ---- እውነተኛ ደስታ ያለባት ብቸኛ ከተማ መሆንዋን በዕምነት ተመልክቶ ነው ።

ከእርሱ ጋር ፣ በእርሱ ከተማ ለመኖር ---- ሊወስደን መምጫው ቀርቦአልና ያለንን አጥብቀን እንያዝ ፣ እንበርታ ። ----

አይመስሎትም ?



# ይሳኮር

" ይሳኮር አጥንተ ብርቱ አህያ ነው
በበጎች ጉረኖም መካከል ያርፋል
ዕረፍትም መልካም መሆንዋን አየ "

ዘፍ 49 ÷ 14

ኑ ! ተሰብሰቡ አላቸው ያዕቆብ ልጆቹን ÷ በኋለኛው ዘመን የሚያገኛቸውን ሊነግራቸው የልቡን ሊያጫውታቸው ፣

ይሳኮር ፦ አጥንተ ብርቱ ጎበዝ ነህ ተባለ ። ጉልበትህ የአህያ ጉልበት ነው ። አቅም አለህ ፣ እውቀት አለህ ፣ ኋይለኛ ነህ ።
ግን ሰነፍ ነህ ፣ እረፍት መልካም መሆንዋን ታያለህ ፣
አቅም ሳያንስህ ---- ስራ አትወድም ፣ ልግመኛ ነህ ።

ይሳኮር በወንድሞቹ መካከል እየኖረ ልግመኛ ነው ። መስራት አይወድም
አቅም ፣ ጉልበት ፣ እውቀት አለው ÷ ግን ሰነፍ ነው ይሳኮር ።

" እኛ ፍጥረቱ ነንና ፣ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን " ኤፌ 2 ÷ 8

እንጂ በወንድሞችና እህቶች መካከል ያለስራ እንድንኖር አይደለም እግዚአብሔር የጠራን ።

# እርሶሳ !

" ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ ! "

ሮሜ 1 ፥ 1

በየማለዳው አያሌ ልብን የሚሰብሩ መጥፎ ዜናዎች የምንላቸው ዜናዎች ደርሰው ይከቡናል ፡፡

መጥፎ ዜና ፤ መጥፎ ነውና ልባችንን ሰብሮ ቀና ብለን እንዳንራመድ ያደርገናል ፡፡

ልብን የሚሰብር ዜና በእርግጥም ልብን ይሰብራል ፡፡ በዚህ ልብን በሚሰብር ዜና መሃል ፤ መጥፎ ዜና መሃል ፥ መልካም ዜናን ማውራት ምን ያህል በረከት ነው ፡፡

መልካም ዜና ፡- ሃጢያትህ ተሰረየችልህ የሚል ዜና ፤

መልካም ዜና ፡- በጌታ ዘንድ ( በሰማይ ) ስፍራ አለህ የሚል ዜና ፥
መልካም ዜና ኢየሱስ ይመጣል እኛም እናርፋለንና በርታ ፤ በርቺ የሚል ዜና ------- መልካም ዜና ፡፡

ሃዋርያው ጳውሎስ ለዚህ መልካም ዜና ፥ ማለትም ለክርስቶስ ወንጌል ተለየሁ ነው የሚለን ፡፡

እርሱን ብቻ ልናገር ለእርሱ ብቻ ሆንሁ ነው የሚለው ፡፡

እርሶሳ ? ለምን ተለይተዋል ?

ወንጌል እኮ መልካም ዜና ነው ፡፡



# " አንተ ግን "

2ጢሞ 3 ፥ 10

ከማንኛውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ ዛሬ በመጨረሻው ዘመን ውስጥ ነው ያለነው ፡፡

ምድራችን በታላቅ መከራ ውስጥ ልታልፍ በሩ ላይ ደርሳለች ፡፡ የሚያስጨንቅ ዘመን የተባለለት ዘመን ላይ ነው የምንኖረው ፡፡

ጦር ፤ የጦር ወሬ የበዛበት ዘመን ፥ ሰዎች ፤ በሰዎች የጨከኑበት ዘመን

መልካም የሆነውን የማይወዱበት ዘመን ፤ የከዳተኞች ዘመን

ከእግዚአብሔር ይልቅ ፤ ተድላን የሚወዱበት ዘመን

የአምልኮ መልክ እንጂ ፤ በእርግጥ እግዚአብሔር የማይመለክበት ዘመን
ታላቅ ክንዱና ኀይሉ የተካደበት ዘመን

ሰዎች እየተማሩ ፤ እውነትን ወደ ማወቅ የማይደርሱበት ዘመን
ይህንንም እውነት የሚቃወሙበት ዘመን
ላይ ነው ያለነው ፡፡ ------------- መቼ ?

አዎን ዛሬ !

ስለዚህ ፡- አንተ ግን ! " በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ፀንተህ ኑር "
2ጢሞ 3 ፥ 14

ጌታ ሊገለፅ ነው ! አንተ ግን ---------------!

# አይደክምም !

" አላወቅህምን ? አልሰማህምን ? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ ÷
የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው ፤ አይደክምም ÷ አይታክትም ÷
ማስተዋሉም አይመረመርም ። "

ኢሳ 40 ÷ 28

የምናደርጋቸው ማንኛቸውም ነገሮች ከኛ ኀይል ስለሚወስዱ አቅማችንን ይቀንሱታል ።

ምናልባት ዛሬ ሃይለኞች ናቸው የምንላቸው ሰዎች እንኳን አንድ ቀን ሃይለኛ ሳይሆኑ እናገኛቸዋለን ።

ሽምግልና በየማለዳው ወደእኛ እየገሰገሰ በመምጣቱ ምክንያት ፤ ትላንት በጉርምስና ስናደርጋቸው የነበሩትን እንኳ እንዳናደርግ ያግዱናል ።

እግዚአብሔር አባታችን ግን ፤ አይደክምም ፤ አይታክትምም ።

ለዚህ ነው ኢሳያስ " አላወቅህምን ? አልሰማህምን ? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ ÷ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው ፤ አይደክምም ÷ አይታክትም ÷ ማስተዋሉም አይመረመርም " የሚለን ።

በትልቁም በትንሹም የእርሱን እርዳታ ለመቀበል ወደኋላ አይበሉ ። አያደክሙትም ÷ አያታክቱትምና ፤ ሃይሉም ሁል ጊዜ የእርስዎ ፤ ለእርስዎ ነውና ።



# ነሑሽታን

" ሕዝቅያስም :- ሙሴ የሠራውን የናሱን እባብ ሰባበረ ፤
ስሙንም ነሑሽታን ብሎ ጠራው ። "

2 ነገ 18 ÷ 4

ከሰባት መቶ ዓመት በፊት የእስራኤል ልጆች በጉዞ ሰውነታቸው በመድከሙ በእግዚአብሔርና በሙሴም ላይ አንጎራጎሩ ። መናን ተፀየፉ ፤ ከግብፅ ለምን ? ወጣን አሉ ፤ ባርነትን ተመኙ ።

ማጉረምረማቸው እንዲነደፍ ፤ እንዲወጋ ፤ ነዳፊ እባብ ተላከባቸው ÷ አለቀሱ ፤ ጮሁ ፤ ነዳፊው እንዲርቅላቸው ለመኑ ፤ ተማፀኑ ።

የናስ እባብ ሰርተህ ከፍ አርገህ ስቀለው ተባለ ሙሴ ፤ ያየው እንዲፈወስ ፤ ከተነደፈበት መነደፍ እንዲነፃ ። ( ዘፀ 21 ÷ 4 - 9 )

ያዩት ተፈወሱ ፤ ነፃ ወጡ ፤ አመለጡ ።

ሰባት መቶ ዓመት ? ሰቀሉት ------ አመለኩት ------ ያንድ ቀኑን የናስ እባብ ÷ የዛን ቀኑን የናስ እባብ ።

ሕዝቅያስ :- ከእግዚአብሔር ጋር የተጣበቀው ( 2 ነገ 18 ÷ 6 ) ሲመጣ በሕዝቡ ልብ የተጣበቀውን የናስ እባብ አስወገደው ነሑሽታን ( ነሃስ ብቻ ) አለው ።

የናሱ እባብ ፤ ነሑሽታኑ ------ ነሃስ ብቻው ! ያንድ ቀኑ --- ላንድ ቀኑ ------ ሰባት መቶ ዓመት ??

ዘላለማዊ ሕይወት የሚሰጠው ፤ ዘላለማዊው ÷ ዘላለም የሚያኖረው ፤ የሚኖረው ( ዮሃ 3 ÷ 14 - 15 ) ------ ምነው ? ምነው ? ------- ምነው ? ገፋነው !

# <u>እንዲሁ --- አደረገ</u>

" ኖኅም ፤ እንዲሁ አደረገ ፤
እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሁሉ እንዲሁ አደረገ ። "

ዘፍ 6 ፥ 22

እግዚአብሔር ኖኅን አዘዘው ኖኅም አደረገ ። ዘፍ 6 ፥ 22
ይህ ነው ኖኅን ልዩ የእምነት ሰው ያደረገው ------- እንዲሁ አደረገ ።

እግዚአብሔር አለ ኖኅ አደረገ ። መፅሃፍ ቅዱስ በማንኛውም ስፍራ ኖኅ ሲከራከር ወይም አለመታዘዝን ሲያደርግ አያሳየንም ።

ደሕንነቱ በእግዚአብሔር ጥበብና ማስተዋል ፤ ቸርነትና በጎነት እንጂ በእርሱ ማንነትና ምንነት ላይ አለመደገፉን የተረዳ ሰው ነበርና ።
እግዚአብሔር እንደገለፀለት እንዲሁ ያደርግ ነበር ።

ለእኛም በዚህ ዘመን ላለነው አማኞች ዝም ብለን ጌታን በቃሉ ብቻ በመታመን ወደፊት እንገሰግስ ዘንድ ለትምሕርታችን ተፅፎልናል ።

ልብ እናድርግ ፤ እንደኖኅ እግዚአብሔርን በቃሉ ታምነን የምናደርገው እርምጃ ሁሉ በእርሱ ዘንድ <u>እንድንታሰብ</u> ያደርገናልና በቃሉ ታምነን እንውጣ ።
" እግዚአብሔርም ኖኅን አሰበ "   ዘፍ 8 ፥ 1



# <u>ፀሎቴ !</u>

" ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ
ለደቀ መዛሙርቱ <u>እንደ ገና</u> ተገለጠላቸው ። "

ዮሃ 21 ፥ 1

ለዘመናት አብረን የተጓዝነው ጉዞ ፤ የነበረን ሕብረትና አንድነት ደርሶ ድንገዝዝ ይልና ያ ! ቀድሞ እርሱንና ክብሩን አይተን የጀመርነው ጉዞ ይጠፋና ----- ዝም ብለን------ እንወጣለን ፤ እንገባለን ።

ከዚህ በፊት ተገልያልናል ------ በሃሴት በደስታ ጉዞ ጀምረናል እያደር ግን ደንዝዞብናል ፤ ትውስታ ብቻ ሆኖብናል------

ደቀ መዛሙርቱ ክርስቶስ ተገልያላቸው ለብዙ ጊዜ በሃይል ተጉዘዋል ፥ ዛሬ ግን ----- ያ ሁሉ ትዝታ ብቻ ሆነ ፤
ዛሬን ሳይሆን ትላንትን ፤ የሚሆነውን ሳይሆን የሆነውን ማሰብና እርሱን ብቻ መተረክ ሆነባቸው ።

የተጠሩበትን ሳይሆን ከዚህ በፊት የኖሩበትን ስራ ለመስራት ወደ ቀድሞ ተግባራቸው ተመለሱ ።

----- አድካሚ ሌሊት ፥ ባዶ ሌሊት ሆነባቸው

በዛ ሌሊት ---  በጭንቁ ለሊት --- በአድካሚው ለሊት ---
ያ ! ጌታ ፤ መጀመሪያ የጠራቸው ጌታ እንደገና ተገለፀላቸው ፤ በፍሙ ዙሪያ መገባቸው ፤ ለታላቁም ተልዕኮ አበቃቸው ።

ኤልያስም ከኤልዛቤል ዛቻ በሸሸ ጊዜ

" የእግዚአብሔር መልአክ <u>ሁለተኛ ጊዜ</u> ( እንደገና ) መጥቶ ዳሰሰውና የምትሄድበት መንገድ ሩቅ ነውና ተነስተህ ብላ አለው ። ኤልያስም በዛ ምግብ ኃይል እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ ድረስ አርባ ቀንና አርባ ለሊት ሄደ ። " 1ነገ 19 ፥ 7-8

ይህ ነው ፀሎቴ ! ---- የኔ ፀሎት ይህ ነው --- እንደገና ኢየሱስ ይገለፅልኝ ዘንድ ----- እንደገና ! እንደገና ! ----- ይገለፅልን ዘንድ ።

አይመስሎትም ?

መገለፁን አይናፍቁትም ?

## ወይስ !

" ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ ። "

ማቴ 28 ፥ 20

ልቡ እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆነው ዳዊት
" እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት
እርስዋንም እሻለሁ ፤
በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ፤ በእግዚአብሔር ቤት
እኖር ዘንድ ፥

ሲል ምን ማለቱ ነው ?

ወደ አዳራሹ ( ቤተ ክርስቲያን ) ልግባና በላዬ በሩ ተዘግቶ ፤
በዛ ለዘላለም ልኑር ነው የሚለው ?
አይደለም !

ምክንያቱም " እግዚአብሔር እጅ በሰራው መቅደስ አይኖርምና "
የሐዋ 17 ፥24

ዳዊት ፦ " በእግዚአብሔር ቤት ለዘላለም እኖራለሁ ። " ሲል
ከሰው ተለይቼ ለብቻዬ እቀመጣለሁ ሳይሆን ፦
ሁል ጊዜ ፤ በማንኛውም ሰዓት በጌታ መገኘት ውስጥ እሆናለሁ ።
ሲሆን ።

ጌታም " ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ " ይለናል ።
እርስዎ በጌታ ፤ ጌታም በእርስዎ መሆንዎን ያስተውላሉን ?

ወይስ ------ ?



## ጴጥሮስ ያችን ሰዐት

" ሰይፍ ይዞ የነበረው ስምዖን ጴጥሮስም ፤
ሰይፉን መዞ የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ ቀኝ ጆሮ ቆረጠ ፤
የአገልጋዩም ስም ማልኮስ ይባል ነበር ። "

ዮሃ 18 ፥ 10

እኔ ? ----- አላደርገውም ! ---------- በፍፁም !
ምናልባት ---- እነዚህ ሊክዱህ ይችሉ ይሆናል እኔ ግን--
" ከአንተ ጋር ወህኒ ለመውረድም ፤ ለመሞትም ዝግጁ ነኝ ። "
ሉቃ 22 ፥ 33

በማለት ለጌታው ያለውን ታማኝነት የገለጠው ጴጥሮስ ፤
ያንን አንደበቱን ተግባራዊ ለማድረግ ሰይፉን መዘዘ ፤ አካል አጎደለ ።

ባለቆመጥ ፤ ባለሰይፉን ቢያቆስል አሰየው ነበር ፤
ግን ምንም መሳርያ ያልያዘውን ተራ አገልጋይ አቆሰለ --- ጴጥሮስ ?

እሰየው ሊባል ፤ ሊወደስ ፤ ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ይልቅ
ቅናት እንዳለው ለማስታወቅ ፈጥኖ አካል አጎደለ ---- ጴጥሮስ ።

ግን ! ምን ተሰምቶት ይሆን ----- ጴጥሮስ
እርሱ የቆረጠውን -- ጌታ ሲጠግነው
እርሱ ያጎደለውን -- ኢየሱስ ሲሞላው

ምን ተሰምቶት ይሆን " ጴጥሮስ ያችን ሰዓት "
እርሱ ------ ያቆሰለበት
ጌታ --------የጠገነበት

ምን ተሰምቶት ይሆን " ጴጥሮስ ያችን ሰዓት "
ጠላቱ ሲፈወስበት ፥ እርሱ ሃፍረት ሲሞላበት ?

ምን ብሎ ይሆን " ጴጥሮስ ያችን ሰዓት ? "

# የተመረጠ ትውልድ

“ እናንተ የተመረጠ ትውልድ ፥ የንጉስ ካህናት ፥ ቅዱስ ሕዝብ ፥
ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ ። ”

1ጴጥ 2 ፥ 9

በየእለቱ ፤ እንደው በየእለቱ ፥ ራሳችንን ስናይ ------
እግዚአብሔር እኛን በሚያይበት ዓይን ማየቱ እንዴት ጠቃሚ መሰለዎ !

“ አክሊል እንደለበሰ ሙሽራ ፥ በጌጥ ሽልማትዋም እንዳጌጠች ሙሽራ ፥
የማዳንን ልብስ አልብሶኛልና ፥ የፅድቅንም መጎናፀፊያ ደርቦልኛልና
በእግዚአብሔር እጅግ ደስ ይለኛል ። ”

ኢሳ 61 ፥ 10

ራስዎን ዋጋ ቢስና ምንም የማይጠቅሙ እንደሆኑ ውስጥዎ ሲሙዋገትዎ
“ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን ፥ ነውርና እድፍ እንደሌለው
እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ ። ”

1ጴጥ 1 ፥ 18-19

ነውርዎ ብቻ ጎልቶ ሲታይዎ ፤

“ ዓለም ሳይፈጠር ፥ በፊቱ ቅዱስና ነውር የሌለን
በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን ። ”

ኤፌ 1 ፥ 4

የተባልንበትን ቃል ለራሳችን መንገር ።

ተስፋ የሚሆን ነገር ሲጠፋ ፤ ደርሶ ኃዘን ሲከበን

“ ወንድሞች ሆይ ፥ ተስፋ እንደሌላቸው እንደሌሎች እንዳታዝኑ ”

1ተሰ 4 ፥ 13

የሚለውን የተስፋ ቃል ለራስ መናገር ምን ያህል ለውጥን እንደሚያደርግ
ራስዎ ይለማመዱ ዘንድ እናበረታታለን ።

ልብ ይበሉ ! የተመረጠ ትውልድ ፥ የንጉስ ካህናት ፥
ቅዱስ ሕዝብ ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን መሆንዎን